# ይድረስ ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር አብይ አህመድ።

የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር ሆነው፣በትረ ስልጣኑን ከተረከቡ፣ጀምሮ ህዝቡ ጆሮውን እርቦት ስለነበረው፣ኢትዮጵያዊነት፣ደጋግመውና፣ከፍ አድርገው ሲናገሩ፣የኢትዮጵያ ህዝብ፣አብይ ሳይሆን፣ነብይ መጣልኝ ብሎ ድጋፉን እንዳሳየዎት፣አለም አይቶታል፡በተለይም የአማራ ህዝብ። ነገር ግን የፓለቲካ ክደት በሚመስል መልኩ ይህንን የህዝብ ፍቅር፣ከቃላት ባላለፈ የተናገሩትን ፣በተግባር ባለማሳየትዎ፣ ህዝቡን ለከፍተኛ መፈናቀል ፣ግድያና ለቅሶ ዳርገውታል።

የዚህ መንስኤ ደግሞ እርስዎ ፣የቀን ጅቦች ያሏቸው፣የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መምህራኖችዎ እንደሆኑ፣ ጠንቅቀው እያወቁ፣ጅቦቹን ሜዳ ላይ ነፃ ለቀው ፣ስለ አንድነት፣ስለ ሰላም፣ማቀንቀን ወይም አገር አረጋጋለሁ ብሎ መኳተን፣ ውሀን በወንፊት እይዛለሁ እንደ ማለት ነው።

ይልቁንስ ህዝቡን ከሚያስጨርሱት፣እነሱን የመያዝ አቅም ከሌለዎት፣ወይም የእናቴን ህልም እውን ባደረጉልኝ ሰዎች ላይ ሆደ አልጨክን አለኝ ብለውም ከሆነ ፣ህዝቡ ራሱን እንዲከላከል፣ ሀቁ በግልፅ ሊነገረው ይገባል።

እነዚህ ወንጀለኞች እድሜያቸውን ሙሉ በሀገሪቱ ላይ ለፈፀሙት ግፍ፣ህግ ፊት ሳይቀርቡና፣የህግን ምንነት እንድያውቁ ሳይደረግ፣ ይቅርታም ሳይጠይቁ ፣እርስዎ እየተነሱ ፣ይቅር እንባባል የሚሉት ፣ በህዝቡ ቁስል ላይ እንጨት መሰንቀር ነው። እርስዎ ይቅር የማለት ስልጣንም ማንደትም የለወትም፣ ከዚህ ባለፈ እሄዳለሁ ካሉም ወንድሜ በእሳት እየተጫዎቱ እንደሆነ ማሳሰብ እወዳለሁ።

የሰው ልጅ ከነህይወቱ ተዘቅዝቆ ተሰቅሎ በደቦ ድብደባ ሲገደል የታየው፣ከስልሳ ያላነሱ የቤት እንስሳት በእሳት የተቃጠሉት፣ ህዝብ እየተፈናቀለ፣ ቤቱ እየታቃጠለበት ያለው፣በእርስዎ አስተዳደር ውስጥ ሆኖ እያለ፣ለመናገርም፣ ለመስማትም፣ለማየትም፣አለመፈለገዎ፣የእርስዎ መንግስት፣ብአደን፣ ቅማንትና ህወሀት፣ በጋራና በምክር አማራውን እየጨረሳችሁት ነው ብለን እንድንጠራጠር፣ መጠራጠር ብቻም ሳይሆን አምነን፣እነሆ አፍ አውጥተን እንድንነግርዎት ግድ ሆኖብናል።

ስለዚህ እንደ አንድ፣ሀገር መሪ፣እየመሩት ያለውን ህዝብ፣የማወቅ መብቱን አክብረው፣ በግልፅ የመናገር ሀፊነትም ግደታም አለበዎትና ከአሮጌ ፓለቲከኞች ከበባና አጀባ ወጣ ብለው ለህዝቡ ጥያቄ አስቸኳይ መልስ መስጠት ይጠበቅበዎታል።

በሌላ በኩል ሰላምና መረጋጋት በሌለበት፣ብጥብጥና ግድያ በሰፈነበት አገርና ህዝብ፣የሚደረግ የህዝብ ቆጠራ፣ አመኔታም ተቀባይነትም ስለሌለው፣ ከተያዘው ተጨፈኑ እናሙኛችሁ፣ውጣ ውረድ ሩጫ፣ቆም ብለው፣የፋሽስት እርዬተ አለም ተከታይና አስፈፃሚ ሆነው እድሜያቸውን ያሳለፉ፣በጥላቻ አይምሯቸውም አከላታቸውም፣በድን ሆኖባቸው፣ከመሸ መጠጊያ ፍለጋ የሚንከራተቱ፣ ከንቱ አደናጋሪዎችን፣ተውትና ራቅ አድርገው፣ለህዝቡ ጩኸት ቅድሚያ ሰጥተው በማድመጥ፣ተገቢውን ምላሽ መስጠት ግድ ይለዎታል እላለሁ።

አብዱ አሊ

2019/02/12